# ጠ/ሚኒስትር አሸብር ዜናዊ

ታሪኩ አባዳማ መስከረም 2004

ላለፉት ሀያ የወያኔ አገዛዝ ዓመታት የጭካኔ በትር ሰለባ የሆኑ ሰላማዊ ዜጎች ቁጥር በቀላሉ የሚሰላ ባይሆንም እንበለ-ሕግ ሰብአዊ መብት ማዋረዱ መርገጡ ግን እነሆ እስከ ዛሬ አላባራም። በአዲስ አበባ የሚፈፀመውን ረገጣ ሳይውል ሳያድር በትኩሱ ለማወቅ ዕድል ቢኖርም በሌሎች የአገሪቱ ክልሎች በምስጢር እስር ቤቶች እየታጎሩ ፣ በየጉድባዎች እየተረሸኑ የሚገኙ ሰላማዊ ዜጎች ግን እሪታቸው የገደል ማሚቶ መሆኑ ቀጥሏል። ዛሬም እሪሪሪሪ ተገፋሁ… የሚለው ኢትዮጵያዊ ድምፅ ከመቸውም ግዜ የበለጠ ጎልቶ እያስተጋባ ነው።

ትናንት ትልቁ ወንጀል 'ነፍጠኛ ፣ ትምክህተኛ' ነበር - እነ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ስማቸው ግን ጎልቶ ከማይታወቅ በሺህዎች ከሚቆጠሩ ተከታዮቻቸው ጋር ውድ ዋጋ ከፍለውበታል። 'ህገ መንግስቱን በሀይል ለመናድ' የተነሱ ተብለው የታሰሩ ፣ የተደበደቡ ፣ የተገደሉ እና ቤት ንብረታቸው የወደመ ዜጎች ቁጥር አሁንም በአሀዝ የሚገለፅ አይደለም። ወያኔ ሆነ ብሎ በሚቀሰቅሰው የሀይማኖት እና የጎሳ አምባጓሮ ውድ ህይወታቸውን ያጡ ፣ ቤት ንብረታቸው የወደመ ፣ የተፈናቀሉ ምስኪን ዜጎች አያሌ ናቸው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ 'አሸባሪ' በሚል ወንጀል የሚታሰሩ ፣ የሚገደሉ እና የሚሰደዱ ዜጎች እጅግ በርክተዋል። 'ፀረ-አሸባሪነት' እንደ ነፍጠኛነት ሁሉ ለወያኔ ጎጣዊ እና ኢ-ሰብአዊ አገዛዝ አልመችም ያሉ ሰላማዊ ዜጎች የሚታደኑበት እና የሚመቱበት ከህጎች ሁሉ የበላይ 'ህግ' ሆኗል። ኢትዮጵያ የምትተዳደረው ደግሞ ጠ/ሚኒስትሩ ራሱ ህግ በሆነበት አገር በመሆኑ እሳቸው አሸባሪ ወይንም 'ነጭ ለባሽ'… ያሉት ሁሉ ለምን እና እንዴት ተብሎ እንኳ ሳይጠየቅ በታማኞቻቸው ይመታል።

በአገሪቱ ያለው አንድ ህግ ነው - እሱም መለስ ዜናዊ ነው። ህግ ተብሎ የታወጀ ማናቸውም ደንብ ከመለስ ዜናዊ ፈቃድ እና ፍላጎት ውጭ ከሆነ ተፈፃሚ አይሆንም። መለስ ህግ በሆነበት ሌላ ህግ የለም።

ለምሳሌ በተፃፈው የወያኔ ህግ መሠረት "አንድ ተጠርጣሪ ወንጀለኛ መሆኑ በህጋዊ ፍርድ ቤት እስካልተረጋገጠ ድረስ ነፃ ነው" ቢልም ቅሉ በዚህ ስርዓት ጠ/ሚኒስትሩ የጠረጠሩት ሁሉ ነፃ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ደረስ ወንጀለኛ ነው። ጠ/ሚኒስትሩ የጠረጠሩትን 'ነፃ' ነህ ብሎ የሚያሰናብት ፍርድ ቤት ይኖራል ብሎ መጠበቅ ደግሞ ህጉን ጠንቅቆ ካለመገንዘብ የሚመጣ የዋህ ግምት።

ሌላ ምሳሌ ልስጥ? አንቀፅ 39 በግልፅ እንደሚደግገው 'ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት እስከ መገንጠል' ይችላሉ። በዚህ አንቀፅ መሰረት የመገንጠል ጥያቄ ማንሳት በጣም ህጋዊ ነው። ይሁንና በተገንጣይነት የሚከሰሰው ኦነግ ዛሬ 'አሸባሪ' ተብሎ አባላቱ እና የተጠረጠሩ ኦሮሞዎች በሙሉ እየተጋዙ ፣ እተገደሉ ነው - ምክንያቱም የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነው መለስ ኦነግ 'አሸባሪ' ነው ስላለ።

ስለ አሸባሪዎች ዝርዝር ሲነሳ አንድ የሚገርመኝን ነገር ልጥቀስና ወደ ሌላ ጉዳይ ልውሰዳችሁ - በወያኔ መገናኛ አውታሮች ተደጋግሞ እንደሰማነው ሻ'ኣቢያ/ኤርትራ በኢትዮጵያ ውስጥ የማያቋርጥ ሁከት ለመቀስቀስ የአሸባሪነት ተግባር ፈፅሟል እየተባለ ነው። ይሁንና የወያኔ ፓርላማ አልቃይዳን እና አልሸባብን ጨምሮ ኦነግ ፣ ግንቦት 7 እና ኦብነግን 'አሸባሪ' ብሎ 'ሲፈርጃቸው' ሻ'ኣቢያን ግን ከቶ ስሙ በዚህ ዝርዝር ተራ እንዲጠቀስ አልፈለገም። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ካስፈለገ ህጉ (መለስ ዜናዊ) ጠቃሚ ሆኖ ስላልታየው ነው ማለት ይቻላል። ይህ ሀቅ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን መለስ የሚጫወተውን የፈላጭ ቆራጭነት ሚና በጉልህ የሚያመለክት ነው ብዬ አምናለሁ።

በወያኔ ፊት 'አሸባሪ' የሚለውን መስፈርት ለማሟላት እንደ ሻ'ኣቢያ በግልፅ የጠላትነት ተግባር መፈፀም አያስፈልግም - በይስሙላው ህግ መሰረት እንኳ ተደራጅቶ የመብት ጥያቄ ማንሳት ግን አሸባሪነት ነው። ወያኔ አሸባሪ ብሎ ዛሬ እንደ አውሬ የሚያሳድዳቸው ንፁህን ዜጎች ለሰብአዊ መብት መረጋገጥ በፅናት የቆሙ ጀግኖች ናቸው የምንለውም ለዚህ ነው።

መለስ ዜናዊ በ'ተጠረነፈው' ፓርላማ ፊት ወይንም መገናኛ ብዙሀን ዘንድ ቀርቦ የተነፈሰው የጥላቻ ወገዛ ሁሉ እንደ ሕግ አንቀፅ ያገለግላል - የወያኔ 'ፀረ-ሽብር' ሰነድ ትርጉሙ እና አፈፃፀሙ አንዳች ወጥነት የሌለው - ይልቁንም የወያኔ ሹሞች በእጀ መናኛ ያሻቸውን የሚመትሩበት ፣ ባሻቸው ግዜ የሚመዙት የበቀል በትር ነው።

ጋዜጠኛ ውብሸት አሸባሪ ነው ፤ መምህር በቀለ ገርባ አሸባሪ ነው ፤ አርቲስት ደበበ እሸቱም አሸባሪ ነው ፤ እስክንድር ነጋም አሸባሪ ነው… በቃ። 'ፀረ-አሸባሪ' ህግ በመደንገጉ ብቻ የመብት ጥያቄ አንግቦ በፅናት

መቆም ከአሸባሪነት ተነጥሎ የሚታይበት ነገር የለም - መብት ረጋጩን ወያኔ እምቢ ለመብቴ ብሎ መሟገት አሸባሪነት ነው። የወያኔን የስልጣን ዘመን ለማሳጠር የሚደረግ ማናቸውም እርምጃ 'አሸባሪነት' ነው።

ከፍ ሲል እንዳመለከትኩት ተቃዋሚ ፓርቲ በሙሉ በፀረ-አሸባሪ መነፅር እይታ radar ውስጥ ነው - ማለትም ተጠርጣሪ ነው ስለዚህ ወንጀለኛ ነው። ነፃ ፕሬስ አሸባሪ ነው ፣ በነፃ መደራጀት አሸባሪነት ነው፣ ቦንድ አለመግዛት አሸባሪነት ነው ፣ ግንቦት ሰባት አሸባሪ ነው ፣ ኦነግ አሸባሪ ነው - እነኝህን ድርጅቶች የሚመለከት ዜና መዘገብ አሸባሪነት ነው ፣ የድርጅቶቹንም ሆነ የመሪዎቹን ስም ተሳስቶ እንኳ መጥራት አሸባሪነት ነው… በወያኔ ራዳር እይታ ይሄ ሁሉ ተጠርጣሪ በፍርድ ቤት 'ነፃ' መሆኑ እስኪረጋገጥ ወንጀለኛ ነው።

ነፃ ምርጫ 'ሽብር' ስለሚያስከትል 'በጥርነፋ' ቁጥጥር ስር ብቻ ይደረጋል - እናም 99.6% ድል አድርጎ 'ከአሸባሪዎች' የፀዳ ፣ ከተጠርጣሪ (ማለትም ወንጀለኛ) 'የጠራ' ፓርላማ ተመስርቷል።

ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ የመብት እና ነፃነት ጥያቄ ለማፈን ያዋጣኛል ብሎ የቀየሰው ስልት 'በፀረ-አሸባሪ' አዋጅ እንዲታጀብ የተደረገው ግን አለምክንያት እንዳልሆነ ብዙዎች ይረዳሉ ብዬ ገምታለሁ። በዲሞክረሲ ካባ ተከናንቦ ለመታየት የዞትር ምኞቱ በመሆኑ 'ሽርክ' ካደረገችው አሜሪካ ጋር ለመመሳሰል ብዙ ይመኛል። የአሜሪካ መንግስት ወያኔን 'ሽርክ' ያደረገው ለአሜሪካ ብሔራዊ ጥቅም ብሎ ሳይሆን ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ስለሆነ እንዲመስል ለማመልከት ይታክታል - እንደ አሜሪካ ሁሉ 'ፀረ-አሸባሪ' ህግ በማውጣት ፣ አሸባሪዎችን በማሳደድ ፣ በማሰር ተባባሪ እና ዘላቂ ወዳጅ መሆኑን ለማስመስከር ይታክታል… ።

አሜሪካ ከአሸባሪዎች ሴራ ለመከላከል ስትል ሶስት ሺህ ዜጎቿን ከቀጠፈው የሴፕተምበር 11 አሸባሪዎች ጥቃት ማግስት 'ፀረ-አሸባሪ' ህግ አውጇለች። የህጉ አቢይ አላማ የመላውን ዓለም አገር ዜጎች ወይም ዕምነት ተከታዮች በማስጠጋት የምትታወቀው አሜሪካ በዚህ አጋጣሚ ሰርገው ሊያጠቋት የሚሹ ድርጅቶችን ሆነ ግለሰቦችን ለመከታተል የሚያግዝ ህጋዊ መሣሪያ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ህጉ የዜጎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል በልዩ ሁኔታ እና የወንጀል ድርጊት ላይ ተፈፃሚ ከመሆን በስተቀር የአገሪቱን ህጎች ተክቶ የሚሰራ አይደለም። ያም ሆኖ አሻሚ ነው በሚል ብዙ ትችት የቀረበበት ሰነድ በመሆኑ አፈፃፀሙ እጅግ ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግበታል - ጭራሽ በኦባማ ዘመን ይህ ደንብ ሲጠቀስ ተሰምቶ አያውቅም።

በዚህ መካከል የምዕራቡ ዓለም በተለይም ደግሞ አሜሪካ ለፀጥታ አስጊ ናቸው ብላ የመዘገበቻቸውን አክራሪ እስላሞች እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ተባባሪ ትሻለች - ወያኔ ይህን የምዕራባውያን ስጋት ተንተርሶ የቅርብ ተባባሪ ሆኖ ቀርቧል። ተባባሪነቱን አንተርሶ ያወጣው 'ፀረ-አሸባሪ' ህግ ግን ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ አይነት መሆኑን ድፍን አለም ያውቀዋል። ይህን በማስረጃ ላሳይ።

እሩቅ ሳንሄድ አልቃይዳ አሜሪካ ላይ ጥቃት ማድረግ ሲጅምር ቦምብ አፈነዳው ኬንያ እና ታንዛኒያ ርዕሰ ከተሞች ላይ በ1998 ኦገስት ነበር። ቢን ላደን ናይሮቢ ላይ ጥቃት ሲሰነዝር ኬንያ በውስጥ የፖለቲካ ውጥረት ውስጥ ነበረች። ተቀዋሚዎች ገዢውን ካኑ ፓርቲ ከስልጣን ለማውረድ ጠንካራ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ወቅት ነበር። ይሁንና ገዢው ፓርቲ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ተቃዋሚን ለማዳከም ሲል 'ፀረ-አሸባሪ' ቅብጥርሴ የሚባል ህግ አላወጣም። አሸባሪዎች በአገር ላይ የሚነሱ እንደመሆናቸው ሁሉም ዜጋ አገሩን ለመከላከል እኩል ሀላፊነት እንዳለበት በማመልከት ጉዳዩ በጥንቃቄ እንዲያዝ ተደረገ።

በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበሩት ዳንኤል አራፕ ሞይ ተቀናቃኞቻቸውን ፀጥ ለማሰኘት መልካም አጋጠሚ ነው ብለው አዋጅ ለማውጣት አልተጣደፉም። ይህ ከቶ ሊሆን ያልቻለበት አቢይ ምክንያት ደግሞ አገሪቱ በማይናቅ ደረጃ የህግ የበላይነት ያለበት በመሆኑ ነው። ጦር ሀይሉ እና የፍትህ ስርዓቱ ከፖለቲካ ፓርቲ ታማኝነት የዘለለ ነፃ ብሔራዊ ቅርፅ የያዘ በመሆኑ ነው። የቢን ላደን አሸባሪ ቀጥተኛ ጥቃት ሰለባ የሆኑት ኬንያ እና ታንዛንያ ብዙ ዜጎቻቸው በጠራራ ፀሀይ ሲያልቅባቸው እንኳ ህጋቸውን መሰረት ያደረገ ህጋዊ ክትትል እና እርምጃ ከመውሰድ በስተቀር 'ፀረ-አሸባሪ' የሚል ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ አላገኙትም - ጉዳዩ የአገሪቱ መሪዎች ለህግ እና ሰብአዊ መብት ጥበቃ ያላቸውን ክብር ያመለክታል።

አሜሪካ አሸባሪ ብላ የምትከታተላቸው ግለሰቦች የሚኖሩት አንድም በቶራቦራ ተራራ አለበለዚያም ፓኪስታን ወይንም በተለያዩ አገሮች ስማቸውን ቀይረው ፣ የውሸት ፓስፖርት ይዘው በስጋት እና በጥንቃቄ ነው። ቀንደኛው ቢንላደን ፓኪስታን ተሸሽጎ ይኖርበት ከነበረው የተንጣለለ ቪላ ድረስ በማሳደድ እንዲገደል መደረጉን እናውቃለን። ቢን ላደን የሚኖርበትን ስፍራ ለማወቅ ዘጠኝ ዓመታት የፈጀ ጥብቅ ክትትል ተደርጓል። የቅርብ ረዳቶቹ እና መልዕክተኞቹ ተራ በተራ ከየተሸሸጉበት እየተለቀሙ ለፍርድ ቀርበዋል።

*ለቢን ላደን/አልቃይዳ በአሜሪካ መንግስት እና በአሜሪካዊ ዜጋ መካከል ምንም ልዩነት የለም። በዚህ አያበቃም - አክራሪዎቸ የሚከተሉት ፀረ-አሜሪካ ጥላቻ አለም አቀፋዊ ባህሪ ቅርፅ እንዲይዝ እና ምዕራባውያን ዲሞክራሲያዊ አገሮች ሁሉ የጥላቻው እና የጥቃት ኢላማ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ። በዳበረው የምዕራብ ዲሞክራሲ ዜጎች ካለ አንዳች ስጋት በነፃ ሀሳባቸውን የሚገልፁበት ፣ የሚፅፉበት ፣ የሚደራጁበት ፣ የፖለቲካ ዕምነታቸውን አለ አንዳች መሸማቀቅ የሚያራምዱበት ነው። በአጭሩ ሰብአዊ ክብር በህግ የበላይነት በማያሻማ መንገድ የተረጋገጠበት ሥርዓት ነው። ሀይማኖት ፣ ዘር ፣ የቆዳ ቀለም ፣ ፆታ ወይንም ፆታዊ ዝንባሌ ሌላውን የማግለያ መሣሪያ የማይደረግበት ሥርዓት ነው። ስለሆነም አሜሪካ እና ምዕራባውያን ላይ ያነጣጠረው አሸባሪነት በዲሞክረሲ እና በነፃ አኗኗር ላይ የታወጀ የሀይማኖት አክራሪዎች ጦርነት ነው - በአሜሪካ ላይ የተነጣጠረው ሽብር በዲሞክራሲ ላይ የተነጣጠረ ጥቃት ነው።*

*ለአሜሪካ መንግስት አሸባሪ ማለት የአሜሪካንን ህልውና ፣ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት እና አኗኗር ለማደፍረስ በሰላማዊ ህዝብ ኢላማ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የተሰለፈ ሀይል ነው። አሜሪካንን ለመምሰል የሚንደፋደፈው ወያኔ አሸባሪ ብሎ የሚያሳድዳቸው ዜጎች የሚያነሱት መሰረታዊ ጥያቄ የአሜሪካ መንግስትና የመንግስታቱ ድርጅት የቆሙለትን የሰብአዊ መብት ድንጋጌ የሚያንፀባርቅ ነው።*

*አሜሪካ እና ወያኔ በፀረ ሽብር አቋም ተባባሪ ናቸው ይባል እንጂ ስለ አሸባሪ እና ሽብር እንዲሁም ሽብረተኞች ያላቸው ትርጉም የሰማይ እና ምድር ያህል ልዩነት አለው። በመሠረቱ ትብብሩ አሜሪካ ስጋት አለ ብላ በምትገምተው የሶማልያ እና መካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ቅርብ ክትትል ለማድረግ እንድትችል ነዳጅ እና ስንቅ ማከማቻ ለመሻት እንጂ ለዋሽንግተን ከዚያ የዘለለ ትርጉም የለውም - ትብብሩ በተመሳሳይ አመለካከት እና አቻ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ቢሆን ኖሮ ወያኔ አሸባሪ ያለውን አሜሪካ አክብሮ ማስተናገድ ባልቻለ ነበር። ወያኔ ይህን ትብብር በአገር ውስጥ የሚነሱ ፍትሀዊ እና ሰብአዊ መብት ጥያቄዎች ለመጨፍለቅ ሲል የሚጠቀምበት መሆኑ ለአሜሪካ ሚስጥር አይደለም።*

*ግልፅነት እና ተጠያቂነት የማዕዘን ድንጋይ በሆነባት አሜሪካ የፖለቲካ መስመሬን አልተቀበለም ተብሎ በአሸባሪነት የሚፈረጅ ድርጅት ወይም ዜጋ የለም - 'ቲ ፓርቲ' የተሰኘው አክራሪ የሪፐብሊካን አንጃ የኦባማን አስተዳደር ጥላሸት በመቀባት እና ዘረኛ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። ህገ መንግስታዊ መብታቸው ነው ተብሎ በፈለጉት ቦታ ስብሰባ ጠርተው ያሻቸውን ቅስቀሳ ያደርጋሉ። በድርጅትነት አልተመዘገቡም ፣ አሸባሪ ናቸው ብሎ የጠየቃቸው የለም - ይሄ ነው ሰፊው ልዩነት።*

*ወያኔ አሸባሪ ብሎ የሚያስራቸው ወይም የሚያሳድዳቸው ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ለመኖር ወስነው ነገር ግን ሰብአዊ ክብራቸው በህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ብሎም በትግል የተሻለ የፖለቲካ አመራር እናመጣለን ብለው የቆሙ ናቸው። ወያኔ 'አሸባሪ' ብሎ የፈረጃቸው በውጭ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ደግሞ በምዕራብ አገሮች ይፋ በከፈቱት ፅ/ቤት እና አድራሻ መሆኑን እናውቃለን። እነ ብርሀኑ ነጋ አሜሪካ ውስጥ አንቱ ተብለው ክብር እና ሞገስ ያለው የጥበብ ሥራ መስክ ላይ ተሰማርተው ህጋዊ እና ይፋ የሆነ ህይወት ይኖራሉ። ብርሀኑ ነጋ አሜሪካ ብቻ ሳይሆን ወደ ፈለገው የዓለም ክፍል በፈለገ ግዜ በይፋ መንቀሳቀስ የሚችል 'አሸባሪ' በሚል ክስ ግን ወያኔ ሞት የፈረደበት ወይም የፈረጀው ኢትዮጵያዊ ነው። ብርሀኑ ነጋ - ቶራቦራ አልተደበቀም ወይም እንደ አሸባሪ ሸሽጉኝ ፣ መታወቂያዬን ደልዙ ሲል አልታየም።*

*እስቲ ገምቱት ወያኔ እና አሜሪካ በፀረ-ሽብር ሽርክና መስርተዋል። አሜሪካ አሸባሪ ያለችው ግለሰብ ወይንም ድርጅት በየትኛውም የአለም ክፍል ቢሸሸግ (ኢትዮጵያን ጨምሮ) መኖሩ ሲደረስበት ፈጣን እርምጃ ይወሰድበታል። ወያኔ አሸባሪ ያለው ግለሰብ/ቦች እና ድርጅት/ቶች ግን ዋና ፅህፈት ቤታቸው ሳይቀር በይፋ አሜሪካ እና በተለያዩ አውሮፓ አገሮች ነው። የድርጅቶቹ መሪዎች በአሜሪካ እና አውሮፓ በነፃ እና ህጋዊ በሆነ ሰነድ ይንቀሳቀሳሉ ፣ ሰርተው ማደር ብቻ ሳይሆን ለድርጅቶቻቸው ድጋፍ ለማሰባሰብ ቅስቀሳ ያካሂዳሉ ፣ ስብሰባ ይጠራሉ ፣ አላማቸውን በይፋ ያስተዋውቃሉ ፣ ድጋፍ ያሰባስባሉ። ወያኔ የሚያላግጥበትን 'ህገ-መንግስት' በሀይል መናድ አስፈላጊ መሆኑን ጭምር በይፋ ያስተምራሉ - ፍትሀዊ ጥያቄ መሆኑንም ይሰብካሉ።*

*በዓለም ውስጥ ተቀዋሚ አሸባሪ የሆነባት ብቸኛዋ አገር የወያኔይቱ ኢትዮጵያ ብቻ ናት።*

*መጣጥፌን በእውቁ ጆርጅ ኦርዌል ጥቅስ ልቋጭ -*

**Saints should always be judged guilty until they are proved innocent.**